# ወደ ግብ ለመሄድ ገንዘብ መቆጠብ ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

በልዩ የባንክ ሂሳብ፣ ነዋሪዎች ቢያንስ $25 የሚሆን ይቆጥባሉ። እኛ—የዲሲ መንግስት—እርስዎ ለሚያስቀምጡት እያንዳንዱ ዶላር በተከማቹ ቁጠባዎች ውስጥ ተጨማሪ $4 እናስቀምጣለን። ከ 6-18 ወራት ውስጥ እስከ $1500 ሲያስቀምጡ፣ እስከ $6,000 የሚሆን በተከማቹ ቁጠባዎች ውስጥ ያገኛሉ ይህም**የእርስዎን $1,500 ወደ $7,500 ያደርሰዋል**። ቁጠባዎችዎን ለኮሌጅ፣ ለተከታታይ ትምህርት፣ ለስራ ስልጠና፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤት ለመግዛት ወይም ትንሽ ንግድ ለመጀመር ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ይህ ፕሮግራም የዕድል ሂሳቦች በመባል ይታወቃል እና በኢንሹራንስ፣ ደህንነቶች እና ባንኪንግ ዲፓርትመንት የቀረበ ሲሆን የሚተዳደረውም በዋና አካባቢ የንብረት ገንቢዎች በሚባል ትርፋማ ባልሆነ የአካባቢ ድርጅት ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

እነዚህ መግለጫዎች በሙሉ እውነት ከሆነ ብቁ ይሆናሉ፡

- በዲሲ የሚኖሩ ከሆነ
- በአሁኑ ሰአት የሚያገኙት የገቢ ምንጭ ካለ። ያ ማለት በስራ የሚያገኙት ገንዘብ ካለ።
- መኪናዎን እና ቤትዎን ሳያጠቃልል፣ በተጣራ ንብረት ውስጥ ከ $10,000 በታች አለዎት። ሌሎች ንብረትዎ የሚያጠቃልሉት በባንክ ሂሳብ ውስጥ ያለዎት ገንዘብ፣ የጡረታ ቁጠባዎች፣ ቦንዶች፣ አክሲዮኖች ወይም የራስዎ የሆነ ዋጋ የሚያወጣ ነገር ነው። የተጣራ ንብረቶችዎን ለመገመት፣ ንብረቶችዎን ይደምሩ ከዛ ከክሬዲት ድርጅቶች ወይም ሌላ አበዳሪዎች ጋር ያሉብዎትን እዳዎች ይቀንሱ። ሞርጌጅዎን ወይም የመኪና ብድርዎን አይቀንሱ።
- የቤተሰብዎ አመታዊ አጠቃላይ ገቢ —ታክሶችን ከመክፈልዎ በፊት ያለው የእርስዎ ገቢ— በቤተሰብዎ መጠን ላይ ተመስርቶ ከገደቦቹ እኩል ወይም በታች ነው። የቤተሰብ ገቢዎን ለማስላት፣ ከእርስዎ ጋር አብረው የሚኖሩ አዋቂዎች ስራ በመስራት ገቢ የሚያገኙትን ገንዘብ ይደምሩ፡፡ ከዚያ፣ ከ 18 አመት በታች ያሉትን ልጆች አጠቃልሎ ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው ከማህበራዊ ዋስትና፣ ከስራ አጥነት፣ ከልጅ ድጋፍ ወይም የጡረታ ክፍያዎች የሚያገኘውን ገንዘብ ይደምሩ። ከዚህ በታች ምልክት ያድርጉ።

| **የቤተሰብ መጠን**(ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውንም ሰው ይቁጠሩ) | **ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ** |
|---|---|
| 1 | $55,750 |
| 2 | $63,700 |
| 3 | $71,650 |
| 4 | $79,600 |
| 5 | $86,000 |
| 6 | $92,350 |
| 7 | $98,750 |
| 8 ወይም ከዚያ በላይ | $105,100 |

## ያመልከቱ።

1. በዋና አካባቢ የንብረት ገንቢዎች (ወይም CAAB) በመባል ከዲሲ መንግስት ጋር አጋር በመሆን የሚሰራውን ለትርፍ የማይሰራ ድርጅት በDCOpportunity@caab.org ላይ በርዕሰ መስመር "DC Opportunity Account" ብለው ኢሜይል ያድርጉ። ቀላል ከሆነ፣ CAAB ጋር በ (202) 419-1440 ላይ መደወል ይችላሉ።
2. CAAB የእርስዎን የማመልከቻ ቅጽ ይልካል።
3. ቅጹን መልሰው ለ CAAB በኢሜይል ይላኩ። በጣም በቅርብ ያሉ ሁለት የክፍያ ደረሰኞችንና ስራ በመስራት ገቢ ካለው በቤትዎ ውስጥ ካለ ከማንኛውም ሰው በጣም በቅርብ ያለ የታክስ ተመላሽን ያጠቃለለ ሰነድ ማቅረብ ያስፈልግዎታል።

አመልካቾች ተቀባይነት የሚያገኙት ፕሮግራሙ እስከሚችለው ድረስ በዙር ነው። ምንም ክፍት ቦታዎች ከሌሉ፣ CAAB በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ ያስቀምጥዎታል። በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ያሉ አመልካቾች ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ሲገኝ ይነገራቸዋል።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. በ 5 የስራ ቀናት ውስጥ፣ CAAB ማመልከቻው ቅቡል እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ለመንገር፣ በኢሜይል ያሳውቅዎታል።
2. ተቀባይነት ካገኙ፣ CAAB ከፋይናንስ አማካሪው በስልክ እንዲገናኙ ወይም እንዲያወሩ ለማድረግ ለእርስዎ የጊዜ መርሃ ግብር ያወጣልዎታል።
3. የፋይናንስ አማካሪው ለእርስዎ የሚሆን ምክር በማቅረብ ለቁጠባዎችዎ የግብ ስም እንዲሰጡ ከእርስዎ ጋር ይሰራል። እንዲሁም በፕሮግራሙ ውስጥ ለተሳትፎዎና በፋይናንስ ሁኔታዎ ላይ የዳሰሳ ጥናት ለመሙላት ስምምነት መፈረም ያስፈልግዎታል።
4. CAAB በእርስዎና በእኛ —የዲሲ መንግስት በጋራ ባለቤትነት የሚንቀሳቀስ የቁጠባ ሂሳብ Citibank ጋር ይከፍታል።
5. በየወሩ ከ 6-18 ላሉ ወራቶች ቢያንስ $25 ለአዲሱ ቁጠባዎ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። በባንኩ በአካል በመገኘት አስተዋጽኦ ማድረግ ወይም ከደመወዝዎ የራስ ሰር ገንዘብ ማስቀመጫ ማዘጋጀት ይችላሉ።
6. ገንዘቡን ለማውጣት ዝግጁ ሲሆኑ ለሚያስቀምጡት እያንዳንዱ $1፣ እኛ ካስቀመጡት ጋር በማዛመድ $4 እናስቀምጣለን። ከ 6-18 ወራት ውስጥ እስከ $1500 የሚሆን ሊቆጥቡ ይችላሉ፣ አጠቃላይ ቁጠባዎች እስከ $7,500 ሲደርሱ እስከ $6,000 የሚሆን በተከማቹ ቁጠባዎች ውስጥ ያገኛሉ።
7. ቀድመው በሂደቱ ውስጥ ለመረጡት ግብ የተከማቹ ቁጠባዎችዎን ይጠቀማሉ!

## ሁሉም ብቁ አመልካቾች ቅናሽ ያገኛሉ?

አይ፣ ክፍት ቦታዎች የተወሰኑ ናቸው እና የሚወሰነውም መጀመሪያ ባመለከተ ሰው ነው።

## ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

- በየወሩ በትንሹ $25 በየወሩ ተቀማጭ ማድረግ አለብዎት።
- የቁጠባ ሂሳቡ በተከፈተ በ 18 ወራት ውስጥ ቢያንስ ለስድስት ወራት በየወሩ አስተዋጽኦ ማድረግ አለብዎት።
- ከተከማቸ ገንዘብ ወጪ ከማድረግዎ በፊት የፋይናንሻል ስልጠና መውሰድ አለብዎት።
- የቁጠባ ግብዎ ላይ ከደረሱ በኋላ ወይም ለአስቸኳይ ጊዜ ገንዘቡን ለማውጣት ፈቃድ ካገኙ ከሂሳብዎ ገንዘቡን ማውጣት ይችላሉ።
- የቁጠባ ገንዘብዎ መዋል ያለበት፡
    - እንደ ዋና ነዋሪ፣ በዲሲ ውስጥ ቤት ለመግዛት
    - ለእርስዎ ወይም ለትዳር አጋርዎ፣ ለቤት ውስጥ አጋርዎ፣ ለአባትዎ፣ ለእናትዎ፣ ለልጅዎ ወይም እርስዎ ላይ ለሚደገፍ ሰው

- እንደ ኮሌጅ፣ የንግድ ት/ቤት፣ ወይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለእርስዎ ወይም ለትዳር አጋርዎ፣ለቤት ውስጥ አጋርዎ ለአባትዎ፣ ለእናትዎ፣ ለልጅዎ ወይም እርስዎ ላይ ለሚደገፍ ሰው ላሉ ሌሎች ትምህርቶችን የመሳሰሉ ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ያሉ ትምህርታዊ ወጪዎች
- ለእርስዎ ወይም ለትዳር አጋርዎ፣ለቤት ውስጥ አጋርዎ፣ ለአባትዎ፣ ለእናትዎ፣ ለልጅዎ ወይም እርስዎ ላይ ለሚደገፍ ሰው እውቅና ወይም ፈቃድ ካለው ፕሮግራም ጋር ያለ የስራ ስልጠና ወጪዎች
- በሚኖሩበት ቤት ውስጥ ትላልቅ ጥገናዎች ወይም ማሻሻያዎች
- በኢንሹራንስ የማይሸፈኑ ከህክምና ድንገተኛ ጊዜ ጋር የተገናኙ ወጪዎች
- ለጡረታ ቁጠባ
- በጡረታ ጊዜ ለክፍያዎች ወጪዎች ክፍያ መፈጸም

**ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?**

መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች ቦታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎ የዋና አካባቢ የንብረት ገንቢዎችን በስልክ መስመር (202) 419-1440 ላይ ይደውሉ ወይም በDCOpportunity@caab.org ላይ “DC Opportunity Account” በሚል ርዕሰ መስመር ኢሜይል ያድርጉ።

**በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**

በእኛ የፋይናንስ ሀብቶች ገጽ እና በእኛ የቤት መግዛት ሀብቶች ገጽ ላይ ስለሌላ እርስዎን ሊረዱ ስለሚችሉ መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ።

**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**

**ይህ ፕሮግራም የሚመራው በዲሲ መንግስት ነው?**

አዎ። እኛ—የዲሲ መንግስት—የፋይናንሻል ደህንነት ለመገንባት በዲሲ ውስጥ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ግለሰቦች እድሎችን ለመፍጠር ተልዕኮ ይዞ የሚንቀሳቀሰው ለትርፍ ከማይሰራው የካፒታል አካባቢ ንብረት ገንቢዎች ጋር አጋር ነን።

**ከሂሳቤ ላይ ለድንገተኛ ጊዜ ገንዘብ ማውጣት እችላለሁ?**

አዎ። በሂሳቡ ውስጥ እየቆጠቡ እያሉ ለድንገተኛ ጊዜ ገንዘብ ማውጣት ይችላሉ።

በኢንሹራንስ ያልተሸፈኑ የህክምና ድንገተኛ ጊዜ ወጪዎች ወይም ባልተጠበቀና ድንገተኛ የገቢ ማጣት ወቅት ለጤና ኢንሹራንስ ፕሪሚየሞች መክፈል ቢኖርብዎ፣ የራስዎን ገንዘብ እንዲሁም የዲሲ የተከማቹ ገንዘቦችን ያጠቃለለ የድንገተኛ ጊዜ የገንዘብ ወጪዎችን ማድረግ ይችላሉ። እነዚህ ወጪዎች ዳግም መከፈል አያስፈልጋቸውም ነገር ግን በ 90 ቀናቶች ውስጥ መደበኛ ተቀማጮችን መቀጠል አለብዎት።

ከቤት መውጣትን ለመከላከልና ከሥራ ማጣት በኋላ የኑሮ ወጭዎች ላይ እገዛን ጨምሮ በሌላ ምክንያት የድንገተኛ ጊዜ ወጪ ከፈለጉ፣ የራስዎን ገንዘብ ብቻ ማውጣት ይችላሉ እንዲሁም በ 12 ወራቶች ውስጥ ሂሳብዎን መመለስ አለብዎት።

## በዚህ ሂሳብ ክሬዲት መገንባት ይቻላል?

በሚያሳዝን ሁኔታ አይቻልም ምክንያቱም ይህ ሂሳብ በእርስዎና በእኛ የጋራ ባለቤትነት ስር ያለ በመሆኑ፣ በዚህ ሂሳብ ስውጥ ገንዘብ ማስቀመጥ የእርስዎን የክሬዲት ነጥብ አያሻሽልም።

## የቁጠባ ገንዘቤን ቤት ለመግዛት ለመጠቀም እፈልጋለሁ። ለፕሮግራሙ ማሳወቅ አለብኝ?

አዎ። በቤቱ ውስጥ መኖር ይኖርብዎታል እንዲሁም የቤቱ መገኛ ስፍራ በዲሲ ውስጥ መሆን አለበት።

## በቁጠባ ሂሳቤ ላይ ከ $1,500 በላይ መቆጠብ እችላለሁ?

አዎ። ከ $1,500 በላይ መቆጠብ ይችላሉ ነገር ግን ፕሮግራሙ እስከ $6,000 ድረስ የሚሆን ብቻ የተዛማጅ ገንዘብ ይሰጣል። ከ $1,500 በኋላ የሚያደርጉት ማንኛውም የአስተዋጽኦ መጠን አይዛመድም። አሁንም ድረስ የምናበረታታዎ እስከቻሉት ድረስ እንዲቆጥቡ ነው!

## ከማዛመዱ በተጨማሪ፣ በቁጠባ ባሂሳብ ውስጥ የማስቀምጠው ገንዘብ ወለድ ይወልዳል?

አይነተኛ ቁጠባ ጥሬ ገንዘብን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ባንክ ውስጥ አስቀምጠው በሚቆጥቡት ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲያገኙ ያደርግዎታል። ይህ ልዩ የቁጠባ ሂሳብ ወለድ አያስገኝም ነገር ግን ከእኛ የሚመጣው ተዛማጅ ገንዘብ በተለምዶ ካለው የወለድ ተመን አቅርቦት በጣም ትልቅ ነው።

## ከዚህ በፊት በፕሮግራሙ ከተሳተፍኩና ተዛማጅ ገንዘብ ካገኘሁ፣ እንደገና መሳተፍ እችላለሁ?

ካሉት ክፍት ቦታዎች ይልቅ በፕሮግራሙ ላይ የበለጠ ፍላጎት አለ ስለዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡትን አመልካቾች ብቻ መቀበል እንችላለን።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*